# በ2002 ምርጫ ህዝቡ ተቃዋሚዎችን

# ለምን ድምፁን ነፈጋቸው?

**ፈንቅል (ከዓለም ከተማ-ሰሜን ሸዋ)**

በ2002 ዓ.ም የተካሄደው 4ኛው አገራዊ ምርጫ በኢህአዴግ ምሉዕ አሸናፊነትና በተቃዋሚዎች ተሸናፊነት ተደምድሟል፡፡ ኢህአዴግ ምርጫውን በአሸናፊነት እንዲወጣና ተቃዋሚዎች ደግሞ በሽንፈት እንዲጨርሱ ያደረጋቸው ሁለቱ አካላት በምርጫ ክርክር ወቅት መሠረታዊ በሆኑ ህገ መንግሥታዊ አንቀጾች ላይ የወሰዷቸው የአቋም ልዩነቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ህገ መንግሥታዊ አንቀጾች የህዝብ ልጆች ደማቸውን አፍስሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው በከፈሉት የህይወት መሥዋዕትነት ፅኑ መሠረት ላይ የቆመውን ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት አክብሮ የመጠበቅና የማስቀጠል ወይም የመናድ ጥያቄ ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ ለህዝቡ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ይቀጥል? ወይስ አይቀጥል? የሚል የህልውና፣ የመብትና የነፃነት ጥያቄ ነበር፡፡

በህገ መንግሥት ሥርዓቱ ላይ የተካሄዱ ክርክሮችና ተቃዋሚዎችም በእነዚህ ክርክሮች በዋናነት በአንቀጽ 39፣ በፌዴራሊዝም አወቃቀር እና በመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ላይ የወሰዷቸውን አቋሞችና ያቀረቧቸውን አስተያየቶች በቅደም ተከተል በማነፃፀር እውን ኢህአዴግ ያሸነፈው፣ ተቃዋሚዎችም የተሸነፉት በህገ መንግሥቱ ላይ በወሰዱት አቋም ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በትኩረት ማየት ተገቢ ነው፡፡

ከህገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 እንጀምር፡፡ተቃዋሚዎች አንቀጽ 39 ኢትዮጵያን የሚበታትን ስለሆነ መውጣት አለበት ይላሉ፡፡ በቅድሚያ አንቀጽ 39 የሚለውን በትክክል መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡ አንቀጹ በህገ መንግሥቱ ውስጥ መስፈሩ ያለውን ፋይዳ በውል ተገንዝቦ ማመዛዘንን ይጠይቃል፡፡

ይህ አንቀጽ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የህልውናቸው ዋስትና ነው፡፡ ከረጅም ዓመታት በፊት ጀምሮ የዘለቁ ሕዝባዊ አመጾችና የትጥቅ ትግሎች መነሻ የነበሩ ምክንያቶችን ስንመረምር በአመዛኙ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የዕኩልነት፣ የመብትና የነፃነት ጥያቄ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ እነኝህ ጥያቄዎችም በአግባቡ ምላሽ ያልተሰጣቸው ስለነበሩ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ብዙዎችን ወደ ትጥቅ ትግል እንዲያመሩ ያደረገ ሁኔታ ፈጥሮ ቆይቷል፡፡ የአፈናና ጭቆና ሥርዓት አለቅጥ በመንሰራፋቱ ምክንያት ለህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሕዝብ ልጆች በወቅቱ የትጥቅ ትግልን እንደ  ዓላማ ማስፈጸሚያ ብቸኛ አማራጭና ስልት በመውሰድ ተጠቅመውበታል፡፡

ከዚህ መሠረታዊ ችግር የሚነሱ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ጥያቄ በእኩልነትና በዴሞክራሲያዊ አግባብ ምላሽ ለመስጠትና ለህዝቦች ነፃነት ህገ መንግሥታዊ ዋስትና ለመስጠት ሲባል ነው አንቀጽ 39 የተቀረጸው፡፡ ይህን አንቀጽም የመላ ኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ተወያይተው ይበጀናል ብለው የቀረጹትና ያፀደቁት በመሆኑ ቅቡልነቱ አጠያያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

አንቀጽ 39 ከፀደቀ በኋላ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ተስማምተው በልዩነታቸው አንድነታቸውን አጉልተውና እጅ ለእጅ ተያይዘው እንደ አንድ ሕዝብ መቆም ችለዋል፡፡ በዚህም የአገሪቱን ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ እያፋጠኑ ይገኛሉ፡፡ አንቀጽ 39 በፈቃደኝነት ላይ ወደተመሰረተ የሕዝቦች አንድነትና እኩልነት እያመጣቸው እንጂ ተቃዋሚዎች እንደሚሉት አገሪቱን ወደመበታተን እያመራ እንዳልሆነ እስካሁን የተጓዝንበት ሂደት ያረጋግጣል፡፡

ይህ አንቀጽ ብሔር፣ ብሔሰቦችንና ህዝቦችን በመፈቃቀድ ላይ ወደተመሠረተ አንድነት ያመጣቸውና ህገመንግሥታዊ ዋስትና የሰጣቸው ነው፡፡ በመሆኑም ህገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ጠብቆ ማቆየት የህልውናቸውና የማንነታቸው መገለጫና ማረጋገጫ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

ህገመንግሥቱን መቃወም የሚያዘወትሩት አንዳንድ ተቃዋሚዎች አንቀጽ 39 ኢትዮጵያን ይበታትናል፤ ከህገመንግሥቱም ሊወጣ ይገባዋል ቢሉም የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት፣ እኩልነትና ነፃነት በተግባር ያረጋገጠና የማንነታቸውና የህልውናቸው ማረጋገጫ ዕኑ መሠረት፣ የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመወሰንን ሥልጣን ያጎናፀፈ ከመሆኑ አኳያ የአንቀጹን ከህገመንግሥቱ መውጣት ህዝቦች በፍፁም አይቀበሉትም፡፡አንቀጽ 39 በሕገ መንግሥቱ ውስጥ መካተቱ አንዳንድ ወገኖች እንዳሉት ወይም አሁንም ድረስ እንደሚሉት ለኢትዮጵያ መበታተን በፍጹም ሰጋት ሊሆን አይችልም፡፡ምክንያቱም የአንቀጹ መኖር ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብትና እኩልነት በተግባር መረጋገጥ እንደ ሚዛን ሆኖ ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና የሚሰጥ ትርጉም ያለው የዝቦች የእኩልነት ማረጋገጫ ነውና፡፡

ሌላው ተቃዋሚዎች የሚያነሱት ነጥብ የፌዴራሊዝም አወቃቀሩን የተመለከተ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የአገራችን የፌዴራሊዝም አወቃቀር በዋናነት መሠረት ያደረገው የብሔር ብሔረሰቦችን ቋንቋ፣ የጋራ ባህል፣ ሥነልቦናና ታሪክ እንዲሁም አሰፋፈር እንደመሆኑ ለብሔር ብሔሰረቦችና ሕዝቦች ማንነት ታላቅ ክብርና ዕውቅና የሰጠ ነው፡፡

ይህ የፌዴራል አወቃቀርም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰንን መብትና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደርን ነፃነት ያጐናፀፈ፣ በመፈቃቀድና በመተማመን ላይ የተመሰረተ አንድነታቸውን ያጠናከረ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ፌዴራላዊ አወቃቀር ከሚከተሉ አገራት መካከልም ህንድ እና ካናዳ ዋነኛ ተጠቃሽ አገራት ናቸው፡፡

ተቃዋሚዎች ከዚህ በተፃራሪ በመቆም ፌዴራላዊ አወቃቀር መኖሩን ተቀብለው፣ አከላለሉን ግን በወንዝ፣ በተራራ፣ በሸንተረር ወዘተ ላይ መመስረት አለበት ይላሉ፡፡ ፌዴራላዊ አወቃቀር በዋናነት መልክዐ ምድራዊ አከላለልን መሠረት ማድረግ እንዳለበት በተደጋጋሚ ያነሳሉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ከሰው ልጅ ይልቅ ለጋራና

ለሸንተረር ቅድሚያና ትኩረት መስጠት በከፍተኛ መስዋዕትነት የተገኘውን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን መብት መናቅ ነው፡፡

ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ፌዴራላዊ አወቃቀሩ መልክዐምድራዊ አከላለልን በዋናነት መሠረት አድርጐ ቢሄድ አንዱ ብሔር ብሔረሰብ በሌላው እንዲዋጥ፣ ተመሳሳይ ባህልና ቋንቋ ያላቸው የአንድ ብሔር ብሔረሰብ አባላት በተለያዩ ክልሎች እንዲኖሩ ወይም እንዲበታተኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች እንዲሆን የሚያደርግና ይህም ለተለያዩ ግጭቶች የሚዳርግ ነው፡፡

ይህን የብሔር ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን ሉዓላዊነትና የማንነት ጥያቄ ምላሽ የሰጠ ህገመንግሥታዊ የፌዴራላዊ ሥርዓት አወቃቀር መቀየር አለበት ማለታቸው ሌላው የተቃዋሚዎችን ሽንፈት የጋበዘ ምክንያት ነው፡፡

በሌላም በኩል ተቃዋሚዎች ህገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ከተቃወሙባቸው መሠረታዊ ሀሳቦች መካከል የመሬት ባለቤትነትን የተመለከተው አንዱ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተቃዋሚዎች መሬት በግል ይዞታ ስር ሆኖ መሸጥ መለወጥ አለበት ይላሉ፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት አርሶ አደሩ የተበጣጠሰ መሬት ይዞ ምርታማ መሆንና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አይችልም፡፡ በተጨማሪም በተበጣጠሰ ማሳ ሜካናይዝድ የሆነ ግብርናን ማካሄድ አይቻልም የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና ላይ ነው፡፡ የአርሶ አደሩ ህይወትም የተመሰረተው በመሬት ላይ እንደመሆኑ የመሬት ጉዳይ እጅግ መሠረታዊ የሆነ የህልውናው መገለጫ ነው፡፡

ተቃዋሚዎች መሬት ይሸጥ ይለወጥ ሲሉ የብዙኃኑ መጠቀሚያና የህይወቱ መሠረት የሆነው አንጡራ ሀብቱ በጥቂት ሀብታሞች እጅ በሞኖፖል እንዲያዝና ከኑሮው እንዲፈናቀል የሚያደርግ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ህዝቡ ይህን አልተቀበለውም፡፡

አርሶአደሩ በተበጣጠሰ መሬት ላይ አርሶ ምርትማ መሆን አይችልም ለሚለው መከራከሪያ መንግሥት አርሶ አደሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ የተሻሻሉ የአስተራረስ ዘዴዎችን በማስተዋወቅ፣ የግብርና ግብአት አቅርቦትን በማሻሻል፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት፣ በሞያተኛ የተደገፈ የግብርና አሠራር ዘዴዎችን በማስተማርና ለአርሶ አደሩ ከፍተኛ የልማት ተነሳሽነት ወዘተ በአደረገው ያላሰለሰ ጥረት አርሶ አደሩ አሁን ባለው የመሬት ይዞታ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ችሏል፡፡ ይህ ጥረትም ውጤት እያሳየ በመምጣቱ ገቢያቸው ከእጅ ወደ አፍ የነበረ በርካታ አርሶአደሮችን ወደ ሚሊዮነርነት አሸጋግሯል፡፡ የብዙዎችን ህይወትም በእጅጉ የለወጠ ተጨባጭ ውጤት እየተገኘ መጥቷል፡፡

ከዚህም ጋር በተያያዘ በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ቀደም ሲል ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ በመሆኑ ይህም ለግብርና ምርት ማደግ የራሱ የሆነ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያበረከተ ይገኛል፡፡ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ማደግም የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ቅድሚያ ትኩረት ባሻገር፣ ለኢንዱስትሪው ሴክተር የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ግብአት መሰረት በመሆኑ ሁለቱን አስተሳስሮ በመሄድ በሂደት ወደ ላቀ ኢንዱስትሪያዊ ዕድገት መሸጋገር እንደሚቻል ዕምነት ሊያዝበት ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ይህ የመሬት ፖሊሲ ሴቶችን ከወንዶች እኩል የመሬት ባለቤቶች እንዲሆኑ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ ችሏል፡፡ የአርሶ አደሩን የመሬት ባለቤትነትና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መታወቂያ ደብተር እየተሰጠ መሆኑም አርሶ አደሩን በመሬት ባለቤትነት መንፈስ የሥራ ተነሳሽነቱንና ምርታማነቱን እንዲያሳድግ የሚረዳ አዎንታዊ እርምጃ ነው፡፡

በሌላም በኩል ተቃዋሚዎች እንደሚሉት መሬት ቢሸጥ ቢለወጥ አርሶ አደሩ ለጊዜያዊ ችግሩ ሲል መሬቱን ሀብታሞች በሚቆርጡለት ዋጋ ሸጦ የህይወቱ መሰረትና ዋስትና ከሆነው መሬት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚነቀልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ይህም ሰፊውን አርሶ አደር ለስደትና ለፍልሰት የሚዳርገው ይሆናል፡፡

ውጤቱም ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል መረዳት አዳጋች አይሆንም፡፡

በአጠቃላይ በኢህአዴግና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ከተካሄደው የምርጫ ክርክር መረዳት የሚቻለው የ2002 ዓ.ም ምርጫ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማስቀጠል በሚፈልጉና በማይፈልጉ መካከል የተካሄደ ፉክክር መሆኑን ነው፡፡ ምንም እንኳ ተቃዋሚዎች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የአቋም ልዩነት ቢኖራቸውም ህዝቡ በመካከላቸው ምንም ልዩነት ሳያደርግ በድምፁ እኩል ቀጥቷቸዋል፡፡ ለዚህም በዋነኛነት ምክንያት የሚሆነው በህገመንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ ያራመዱት አንድ ዓይነት አቋም መሆኑ ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ህገመንግሥታዊ ሥርዓቱ እንዳይቀጥል ቢፈልጉም ህዝቡ ህገመንግሥቱን ጠብቆ የማቆየትና ህገመንግሥታዊ ሥርዓቱን የማስቀጠል ፍላጎትና ቁርጠኝነት ስላለው በድምፁ ውሣኔውን ሰጥቷል፡፡